# ልወደስ ያለች እጇን ቆርጣ ጣለች

ከጎሹ ገብሩ

ይድረስ ለአቶ አማረ አፍለ ቢሻዉ በቅርብ ግዜ “ከጋምቤል እስከ ሁመራ” በሚል ርዕስ መፅሃፍ አሳትመዋል። ጤና ይስጥልኝ እንደምን ይሆናሉ:: እኔ ቸሩ መድሃኒ ዓለም ይመስገን እጅግ በጣም ደሕና ነኝ። በመጀመርያ ደረጃ ይሕን መጽሐፍ አሳትመዉ ለንባብ በማብቃትዎ እንኳን ደስ ያሎት። በተለይ ባሁኑ ዘመን የታሪክ ብረዛ እንደ አሸን በበዛበት የግለሰብና የመንደር ትረካ እየጎላ፣ ኢትዮጵያ አገራችን በመላዉ ዓለም ዙርያ እንድትከበርና ስመ ጥሩ እንድትሆን አጥንታቸዉና ደማቸዉን ከስክሰዉ ያቆዩልን የጀግኖች ስም እየከሰመና ዝነኛ ታሪክ እንዳልነበራት አስመስለዉ በመካድ፦ያ የተሰራዉ ጀብድ ሁሉ ለማረሳሳት ብዙ ደባዎች በሚዉጠነጠኑበት ወቅት፦ዉነትንና ቅንነት የተመረኮዘ መርህ ተከትሎ ሃቁን ፍርጥርጥ አድርጎ ለህዝብ ማስተማር አማራጭ ሊገኝለት የማይችል መልካም አርአያ ነበር:: ግን አለመታደል ሆኖ ግርፊያችን ጠላት ላይ ማዋል ሲገባን ተንደርድረን ቅድሚያ ወገን ላይ ካላሳረፍን ዐይናችን አይከፈትም። ምንም እንኳ መጽሃፉን ገልጨ ሳነበዉ ከመጀመርያዉ እስከ መጨረሻ ድረስ አዲስ የሆኑ የግልዎ ሃሳብ በብዛት ሳይጨምሩ የብዙ እገሌዎች ሥም መጽሃፉን ቢያጣብቡትም ብዙ የረሳሁት ነገር ለማስታወስ ችያለሁ። መቸስ ፀሃፊ የደከመበትን ስራ ሁሉ አሚልቶ ለማቅረብ ዘዴ መዘየዱ አስፈላጊ ነዉ። በፃፉት ፅሁፍ ውስጥ የብዙ ሊቃዉንቶች ስም በመጥቀስና ያበረከቱት ሞያና የጻፉትን ታሪክ በማስተዋወቅዎ አንብቦ ለማያዉቅ አንብቦ እንዲረዳ፣ረዘም ላለ ግዜ የረሳዉን ዳግም እንዲያስታዉሰዉ በማድረግዎ ይበርቱ የሚያሰኝ ነዉ። ለወደፊቱም ለማሳተም ባቀዱት መፅሃፍም ጤነኛና ትምህርት ሰጭ የሆኑ ሃሳቦች እንደሚያስነብቡን ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ:: የከርሞ ሰዉ ይበለን።

ዛሬ ይሕን ጽሑፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት በቅርቡ ግዜ ለንባብ ካበቁት መጽሐፍዎ ዉስጥ ግልጽ ባልሆነ አነጋገር በጥፋትኛነት ስለከሰሱኝ መልሴን ልስጥበት ብዬ ነዉ እንጅ በአሁኑ ወቅት ሌላ ብዙ አንገብጋቢ የጋራ ጉዳዮች እያሉን አማርኛ አስተካክለሕ አልጻፍክምና በሕዝብ ፊት ለሕዝብ አቅርቤ ጎንደሬነትሕን አሰርዘዉ አለሁ ብለዉ በመነሳትዎ የሚያስቅም የሚያሳዝንም ነዉ። የወላጅ አባቴን ታሪክ ለማግኘት ጠመዝማዛ ጎዳና ከመሄድ ይልቃ የምኖርበት አካባቢና ተሌፎን ጠይቀዉ ቢገናኙኝ ኖሮ የበለጠ ያምር ነበር ። ለሁሉም ነገር ኋላ እመለስበት አለሁ?

*ሥለ ክቡር አባቴ ቀኛ/ገብሩ ገ/መስቀል አስመልክቶ አጠር ባለ ሃሳብ የገለጹት ሁሉ ትክክለኛ የቃል ምስክርነት ለሰጠዎት(ችዎት)እግረ መንገዴን ላመሰግን እወዳለሁ:: እርስዎም የተነገረዎትን ቃል በሙሉ ሳይቀንሱና ሳይደምሩ ስላስነበቡት ይበል የሚያሰኝ ነዉ። ከተባለ አይቀር እኔም አንዳንድ ሳይገለፁ ተረስተዉ የቀሩትን ለመጠቆም ያህል፦የወያኔ ልኡካን የሆኑት ስለ ወልቃይት ታሪክ ለማወቅ መጣን ይበሉ እንጅ አመጣጣቸዉ ለዚህ ጉዳይ አልነበረም:: ዋናዉ ምክንያት እንደ አባቴን የመሳሰሉት ታሪክ አዋቂዎችን በጥቅም ደልለዉ ወልቃይት ትግራይ ናት ብለዉ እንዲመሰክሩላቸዉ ነበር እቅዱ:: ነገር ግን መስቀለኛ ጥያቄ ነበር የገጠማቸዉ። ቀኛዝማች ለወያኔ መልእክተኞች የሚገባቸዉ መልስ ከሰጧቸዉ በኋላ፦በንዴት የተነሳ የእግራቸዉን መዳፍ መሬት ላይ እያጋጩ “ልጆቼ ምን ይሆናል! እድሜ ተሻማኝ! አረጀሁ እንጅ?!” የሚል ቃል እንደተናገሩ፦ከወያኔ መልእክተኞች አንዱ “ባያረጁስ ምን ያደርጉ ነበር?” ብሎ ሲጠይቃቸዉ፦ በንዴት አነጋገር “አንተ ወያኔ---ተከዜን አትሻገራትም ነበር!” በማለት ፊታቸዉ በቁጣ እንደታሰረ ወያኔዎቹን ሳይሰናበቱ ለሚካኤል ጠበል ወደ ተጠሩት እንግዶቻቸዉ ሂደዉ ተቀላቀሉ። ተጋባዡን እንግዳ ከሸኙ በኃላ ግን፦ከንዴት የተነሳ በሽታቸዉ ተቀስቅሶ እስከ ዕለተ ሞታቸዉ ይሰቃዩ እንደነበር አዉቃለሁ። ለመጨረሻ ግዜ እኔን ሲሰናበቱኝ የሰጡኝ ምክርና ወቀሳ፦እንዲሕ እያሉ ነበር: መቸስ የዘመኑ ልጆች ወላጅ ሲመክራችሁ ምክሩን እንደማትቀበሉት ይገባኛል፦ እኔ ግን ከመናገሬ ወደ ኋላ አልልም፦ይሉና

እንባ እየተናነቃቸዉ ይህች ኢትዮጵያችን ባትረገም ኖሮ እንደ ደሮ ብልት ገነጣጥለዉ ለሚያጠፏት ተኩላዎች እግዚአብሔር አሳልፎ ባልሰጣት ነበር። የዛሬ 25ዓመት አንተን፣ ወንድምህንና ጓድኞችህን ምን ብዬ እንደ መከርኳችሁ ታስታዉሰዉ አለህ? ብለዉ ይጠይቁኝና፦ቀጣዩን ማብራርያ አሰሙኝ። ደርግ ማለት አልፎ የሚሄድ የጎርፍ ወሃ ማለት ነዉ። እነዚሕ ተኩላ መሳዮች ትግራይ መሬት የሚንቀሳቀሱት ግን እናንተን ያጠፏችኋል ኢትዮጵያንም ለዉርዴት ይዳርጓታል ብዬ አስጠንቅቄያችሁ ነበር። ይህ አይነት ችግር እንዳይፈጠርም መፍትሄ ብዬ የገመትኩት ሃሳብ ቃሉ እንዲህ የሚል ነበር። የሁለታችሁ (የእናንተና የወያኔ) ችግር ሊፈታ የሚችለዉ በሽምግልና ብቻ ነዉ። ስለዚህ በእኛ በወልቃይት በኩል 50ቀሳዉስቶች በየደብሩ መርጠን እንወክል በትግራይ አካባቢ ደግሞ እንደዚሁ 50ቀሳዉስቶች ወክለዉ መስቀላቸዉን ይዘዉ ተከዜ አማካኝ መገናኛ ፈጥረን እናስታርቃችሁ ከዝያ በኋላ ሁለታችሁ በመተባበር ይሕን የጋራ ጠላታችሁ የሆነዉ ደርግን መጣል አለባችሁ እንዲህ ካላደረጋችሁ ግን እነዚህ ምስጦች ይህችን የታሪክ መፈጠርያ የሆነችዉ አገራችን እንደሚያጠፏት አትጠራጠሩ፤ ማንን ተማምነዉ እንደተነሱስ ለመሆኑ ይረዳችኋል? ኢትዮጵያን የሚጠሉ አረቦች ከጎናቸዉ አድርገዉ ነዉ ስል አንተም በሰላዉ ምላስህ ፦እኛም ሕዝባችን ተማምነን ነዉ? ስትለኝ የትኛዉ ይህን ጌታዉ የበዛ ድህ ሕዝብ፤በሉ ቀልዱ፤ አንድ ቀን አባታችን ምን ብሎን ነበር የምትሉበት ቀን እሩቅ አይሆንም ብያችሁ ነገሩ ሳንቋዋጨዉ እኔም ዳዊቴን ማንበብ ጀመርኩኝ እናንተም ሄዳችሁ ብለዉ ከልባቸዉ አዝነዉ ወቀሱኝ። እኔ እንደሆንኩ የእድሜ ባለፀጋ ነኝ ማድረግ የሚገባኝን ሁሉ በስዓቱ ግዴታየን ተወጥቸ አለሁ። ግን እናንተ ልጆቼ ለስደትና ለመከራ መጋፈጣችሁ ከልቤ አዝናለሁ። ቅድመ አያቶቻችሁ፣አያቶቻችሁና ወላጆቻችሁ ብዙ የደም ዋጋ ከፍለን ያቆየንላችሁ ባድማ ጉልበተኞች ቀምተዉ በአካባቢዉ እንዳትደርሱ ከለከሏችሁ። እስቲ ይታያችሁ ቤት ለእንግዳ ብለን ስላስተናገድንና ስላጎረስን ከመኖርያ ቤታችን ገፍትረዉ እንዴት ያስወጡናል? በማለት በጣም ነበር ያዘኑት። ያ መላዉን ዓለምን የፈጠረ ጌታ ፍርዱን ይሰጣል ከልብ ከለመናችሁት ብለዉኝ ዳግም ሳንተያይ እንደተለያዩን ቀረን። ለወደፊቱ ግዜና ስአቱ ሲፈቅድልኝ ታሪካቸዉን ሰፋ አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

**እስቲ ልተንፍስ ሁሉም ያዳምጠኝ**
**ተበድዬ አለሁ ስላጎረስኩኝ**
**አልጋየን ለቅቄ ስላስተናገድኩኝ**
**ማለዳ ተነስተዉ ና ዉጣ አሉኝ**
**ዋ!ብየ ቀረሁ መላዉ ጠፍቶብኝ።**

**እረ የረገመሽ ከቶ ማን ይሆን**
**በወንድ ልጅሽ አልታደልሽ-በሴቷ ጭምር**
**ሽጣሽ አረፈች ለማይረባዉ ባል**
**ለወለዳቸዉ ማፈርያ የሚሆን**
**ጥናቱ ይስጥሽ አንች የወላድ  መካን**
**የልጅ ልጅ ሲያጠፉሽ -ዳግም ለማየት በቃን**

**አባ በለዉ ተድላ ያገር ኩራት**
**ያለፈዉ የጣልያኑ አልበቃ  ብሎን።**
**እሪ አለች መንደርህ አጋር ጠፍቶባት**
**ስንቱ ጀግና እንዳልተወለደባት**
**ባንዳ እንደልቡ እንዴት ይፈንጭባት**
**እርከን እግር ሰዶ እንዲህ ሲያዉካት**
**ባድማዉ ሙጃ አበቀለ አራሚዉ ሞቶበት።**
**ወልቃይት ምጧ በርትቷል**
**ሁላችን እንፀልይ እንማለል**
**ባል ተብዬዉ ጭራቅ ሆኗል**
**ሕፃን፣ ሽማግሌ በገፍ የሚገድል**
**ለመሬቷ፣ ለሃብትና ንብረቷ ሲል።**

በንያ ባለፉት ጀግኖች ልጆችሽ
ለብዙ አመታት ተከብረሽ ቆይተሽ
ለቸገረዉ ሁሉ በርሽን ከፍተሽ
ለራበዉ ለጠማዉ -እህል ዉሃ ስላቀረብሽ
የደረቀዉ አንጀት -ጠግነሽ ስላዳንሽ
ሞት ሲያንሳት ነዉ ይበሉሽ?

የጎንደር አምበሳ ምነዉ ድምፁ ጠፋ
አንድ ወንድ ታጥቶ እንደ መይሳዉ ካሳ
የአዜብ ቅልብ አይጥ ፒያሳ ላይ ሲያገሳ።

የሁመራ ዋልካ የጀግኖች ንብረት
ሰሊጥ፣ጥጥና ማሽላ ብዙ የሚያመርት
ተባዮች ተራብተዉ ሻግቷል መሬቱ
ስራ ሥሩን ለቀመዉ ስለጨረሱት።

አሁን ቢቀሙን በመሳርያ ጋጋታ
ድርሻችን እኮ ነዉ የማታ የማታ
መሬትን ተሸክመዉ አይወስዱት
በቅርጫት ወይንም ባኮፋዳ
በርትተን እንታገል እስከ ደም ጠብታ።

ተከዜ ያፈራቸዉ ጨካኝ ፋሽሽት
ከአዉሬ እንጅ ከሰዉ ያልተፈጠሩት
ሰዉን እንደ እንሰሳ አጋድመዉ የሚያርዱት።

ጎንደሬዎች ለወያኔ መች ልጃቸዉን ዳሩ
አለሌ ወልደዉ ነዉ እንዲሕ የከሰሩ።

*አቶ አማረ በይበልጥ እንዲረዱት የምፈልገዉ ነገር ቢኖር፡-ከእኔ የበለጠ ጎንደሬነት ላሳር ነዉ ብየ የምመጻደቅ ሰዉ ነኝ፡-ጎንደርን ከበክር ልጇ ከወልቃይት ጋር ለማዋሃድ ከሚጥሩት ተቆርቋሪ እዉነተኛ ጎንደሬ እንጅ ዲቃላዉ አለመሆኔ እንዲገነዘቡት ምንም እንኳ ይህ አባባል ለሚያስተዉል ገንቢ ቃል ባይሆንም ለወቀሱኝ ወቀሳ ግን መልሱ ተስማሚ ነዉ። የጎንደር ልማትም አትደግፍም ነበር ላሉት ክስ መልሴ የሚሆነዉ፡-የት ሆነን ነዉ የምናለማዉ?ጉልበተኞች መሬታችንን በከላሽን ኋይል ቀምተዉ ተከዜን አሻገሩት፡-ጎንደር አካባቢ እንዳናለማም ወያኔዎች ከአሜሪካ ለሄዱት አድር ባዮች፡- መሬቱን በገፍ ስለቸረቸሩት በማይረቡ ጉጆዎች ከተማይቱን አጣበዋታል፡-እዚሁ አሜሪካ ዉስጥም ቅን አሳቢ የጎንደር ተወላጆች የሰበሰቡት የመረዳጃ ገንዘብ፡-ዶክተር ተብየዎች የክፉ ቀን መዉጫ አድርገዉት ተዝናንተዉ ጠያቂ አልባ ቁጭ ብለዋል፡- እርስዎም እንደሆነ የግራ ጉንጫችሁ ቢመቷችሁ የቀኙን ስጡ እያሉ ስለ ሰላም እያስተማሩ ነዉ። ሰላም ማለቱ ባልከፋ ነበር ተጠቃሚዉ ግን አያ መለስና ግብረ አበሮቹ ብቻ ናቸዉ። ይህ አይነት አዲስ ሃሞት አፍሳሽ ሰበካ ወያኔ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አሳፍራ የላከችልን የአፍዝዝ አደንዝዝ የሚያስተኛ ፍቱን መድሃኒት ነዉ። ጎንደር እንዴት አድርጋ እንደምትለማ መላዉ ጠፍቶብኝ እኮ ነዉ ሜዳ ላይ ቆሜ የቀረሁት እንጅ ለጎንደር ብልፅግና ወደ ኋላ የምል አይደለሁም። እስቲ መሬት ሳይኖረን በማልማት እርስ በራሳችን ከምንካሰስ፡-መጀመርያ የተሰበረዉን ወገቧ ጠግነን ጤነኛ ሁና እንድትራመድ መፍትሄዉ ሁላችን

*ተባብረን እንሻላት የሚከፋፍለን መች አጣን ብለዉ ነዉ? ለዚሁ እኩይ ተግባርማ ዶክተሩ ወያኔ አለልን ሌላ ባላስፈለገን ነበር።*

***የት የነበረች ናት ክንፈ ሰባራ ወፍ***
***ከዛም ዘዉ ከዛም ዘዉ ስትል ያየኋት***
***ያለቦታዋ ገብታ ምን አስለፈለፋት።***

** ያለ ዲሞክራስያ፦ሌላ መፅሀፍ ያነበቡ አልመሰለኝም ላሉት፦ልክ የክብር ወርቅ መዳልያ እንደሸለሙኝ ቆጥሬዉ አባባልዎን በደስታና በኩራት ተቀብዬዉ አለሁ:: ምክንያቱስ ቢሉኝ? ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ ንሮን ለማምጣት፦ ከበዝባዦች፤ ከፋሽሽቶችና ጠባብ ብሄርተኞች መንጋጋ ነፃ ለማዉጣት ጀግኖች ባፈሰሱት ቀይ ደም የምትፃፍ ክቡር የሕዝብ መፅሄት እኮ ናት? ሥለ ሰላም እያስተማሩ በጎን ግን ሕዝቡ እርስ በራሱ እንዲፋጅ ጥላቻ የሚነዙትስ ምን እንበላቸዉ? ዲሞክራስያ ወያኔና መሰሎችዋ ሕዝባችን ላይ የሚያደርሱትን ሰቆቃና ስቃይን የምታጋልጥ፦መረገጥና መገረፍን እንደ ልዩ የእግዚአብሔር ስጦታ አድርጎ እንዳይቀበል የጫኑበት ቀንበር አዉልቆ በመጣል፦የመብቱ ባለቤት እንዲሆን የምታስተምር እስከ አሁን ድረስ ተወዳዳሪ ያልተገኘላት የጭቁኑ ሕዝብ ድምፅ የምታስተጋባ እንጅ የወይን ወይም የኢሰፓ አጫፋሪዎች ልሳን እንዳልሆነች እርስዎም የሚስቱት አይመስለኝም።****በጨለማዉና በቀዉጢዉ ግዜ የት እንደነበሩ የማይታወቁ ግለሰብዎች መስመር ዘለዉ በጀግኖች መቃብር ላይ ቆመዉ ያልተደረገዉን ነገር አስመስለዉ የጀግኖችን ታሪክ ለማጉደፍ ለሚሯሯጡት ታሪክ በራዦች ትእግስቱ ስለማይኖረኝና የትዉልዴ ታሪክም ስለሆነ መልስ የመስጠት ግዴታ አለብኝና*** *ስለ አንቀፅ #39 መወለድ ኢሕአፓ ተጠያቂ ነዉ በማለትዎ - አምናለሁ ወያኔ ልዩ ስጦታ አዘጋጅታ እንደምትጠብቅዎት አልጠራጠርም። ወያኔ አገር ወዳዱን የሚከስላትና በሃሰት የሚወነጅልላት በጣም ትፈቅደዋለች ቀይ ምንጣፍ ዘርግታና ሻምፓኝ አዘጋጅታ ቤት ለእንግዳ እያለች ነዉ:: ሳይዉሉ ሳያድሩ የአዉሮፕላን ትኬትዎ እንዲያስቆሩጡ ግም ለግም አብሮ ያዝግም።*

*እንደ እርስዎና መሰሎችዎ የመሳሰላችሁ መንፈሰ ደካማዎች ትግል ለምኔ በማለት ጣጥላችሁ ወይንም ሳትጀምሩት ገና በርቁ ብዙ ምክንያቶች እየደረደራችሁ የግል ንሯችሁን ብታራምዱም ብዙ የእናንተ እድሜ አኳያ የሆኑ ጀግኖች የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ደከመን፤ አረጀን፤ ሰለቸንና ግዜዉ ረዘመብን ብለዉ ሳይርበተበቱ የተጀመረዉን ትግል ግቡ እስኪመታ ድረስ በቆራጥነት እየታገሉ ነዉ። እዉነት እንናገር ከተባለ ኢሕአፓ ከወጣትነት እድሜአችን ጀምሮ ያስተማረን ነገር ቢኖር በእኩልነት የተመሰረተች ኢትዮጵያ ለመገንባት እንጅ በክልል፤ በጎጥ፣ በሃይማኖትና በዘር ከፋፍሎ እርስ በራሳችን እንድንፋጅና መሬታችን ለባእዳን አሳልፈን እንድንቸበችብ ለማንም የይለፍ አረንጓዴ መብራት ምልክት አልሰጠም። ለማስረጃ ያህልም አሁን ወያኔ ለሱዳን የሸጠችዉ ለም መሬት ኢሕአፓ በአካባቢዉ ይንቀሳቀስ በነበረበት ግዜ ተስፋፊዋ ሱዳን በአካበቢዉ እንዳትደርስ አድርጎ ጠረፉን አስከብሮ መቆየቱ እርሶ በቦታዉ ባይኖሩም ካለፈ በኋላ በጀግኖች አፍ ሲወራ ሳይሰሙት የቀሩ አይመስለኝም:: ታድያ የግል ጥላቻ ከለለዎት ይህን አይነቱ እዉነታ በመፃህፍዎ ሳይጠቅሱት እንዴት ያልፉሉ ። ታሪክ አስተምራለሁ ብለዉ የተነሱ እንደመሆንዎ መጠን የግል ቂምን አንተርሰዉ የሚፅፉት ሃቅን ያልተመረኮዘ ወቀሳ የደራሲነት ክብሮን ይቀንሰዋልና እዉነት ለመናገር ቆርጠዉ ይነሱ እላለሁ። ብዙ ግዜ እንደታዘብኩት ለወያኔ መስገድ የከጀሉ በሙሉ ለአንድነት የቆሙትን ድርጅቶች በተለይ ወያኔ የሚፈራቸዉን አጥብቀዉ መኮነን ያበዛሉ:: ከእንደዚሁ ዓይነት የልክፍት በሽታ የሚያምኑት የሲያትሉ ቅዱስ ገብርኤል ይጠብቅዎት። አሰርቱ የጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ቃላትም አንድ አንኳ ሳያጎድሉ ሁሉን አክብረዉ ካልተጓዙ ድካምዎ ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆን። ከትእዛዞቹ ሁለቱን ለምሳሌ ለመጠቆም ያህል በሃሰት አትመስክርና አታመንዝር የሚለዉን አሟልተዋላ ወይ?። ለምሥል መፅሃፍ ቅዱስ ተሸክሞ መታየቱ ብቻ ከኩነኔ ሊያድን አይችልም:: ነገር*

ግን ልቡን ንፁህ  አድርጎ ለሚፀልይ ሁሉ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም በደል ይምረዋልና ትእዛዙን ሁላችንም እናክብር:: ያልተደረገዉና ያልተባለዉ አስመስሎ መክሰስ ትልቅ ሃጢያት ነዉ።

**ሃሰት ለመናገር አትሻም ምላሴ**
**ለዉነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነብሴ(ብሏል እኮ ንጉስ ጥላሆን ገሰሰ)**

*ሁለት የሚቃረኑ አስተያየቶች በእኔ ላይ ፅፈዋል፤ 1ኛ/ወያኔን የማይወዱ ለመሆናቸዉ 100% ላረጋግጥ እወዳለሁ ይሉና፦ነገር ግን ሕዝብ ከሕዝብ የሚያለያዩ ወያኔያዊ ቃላቶች ሳያስቡት ሾልኮባቸዋል ብለዋል። በ1999 ከአስር ዓመት በፊት ወላጅ አባቴ በፀና ታመዋል ሲባል ለሦስት ሳምንት ያህል ጎንደር ህጄ ሳለሁ ከተለያዩ ሰዎች አንዳንድ ስሞታዎችና ቅሬታዎች ሰምቶ አለሁ። ቅሬታቸዉም እንዲህ የሚሉ ነበር: ወያኔ ተወልደን ካደግነበትን ቦታ በአረር ጥይት እየጠበሰች ዘራችን ለማጥፋት ስትገድለን በረን ወደ ክፍለ አገር ከተማችን መጣን፦ ሌላ የምንጠጋበት አማራጭ ቦታ አልነበረንም፦ እዚሕ እንደደረስንም ፦አቀባበሉ እንደ ጠበቅነዉ ሆኖ አላገኘነዉም፦ ወያኔን በሚያዩበት ዐይን ነዉ የሚመለከቱን፦ ከሁለት ያጣ ጎመን ሆነናል ሲሉኝ የሰጠኋቸዉ ምክር ረጋ በሉ የከተማዉ ኗሪ ሕዝብ ወዶ እንዳይመስላችሁ የንሮዉ ዉድነት እየናረ ስለመጣበት ከመደናገጡ የተነሳ እንጅ እናንተን በመጥላት አይደለም ብዬ አሳመንኳቸዉ እንጅ ነገሩ እንዲባባስና ልዩነቱ እንዲሰፋ ወያኔያዊ የመከፋፈል ተንኮል እንደማልሞክረዉ ሳያዉቁ የቀሩ አይመስለኝም። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከታናሽ እሕቴ አፍላ ሃዘን ላይ ስለደረስኩ በርከት ካለ ሕዝብ ጋር ስለ ሁኔታዉ ተወያይተናል። ምክሬም በአክብሮት መቀበላቸዉ በደስታ ገልፀዉልኛል። እኔም ወደ አሜሪካ እንደተመለስኩ የጎንደር ምሁራን ሆይ ከእንቅልፋችሁ ንቁ ወያኔ በወገናችሁ መሃል ጣልቃ እየገባች ጥላቻ እንዲሰፍን መርዟ እየረጨችብን ነዉ። ሥለዚህ ይህን ለማስቆም ሃላፊነት አለባችሁ ብዬ መናገሬ የሚያስመሰግን እንጅ የሚያስወቅስ መሆን አልነበረበት። ሚለንየም ጎንደር ብለዉ ለሚጠሩት ስብሰቦችም አራቱን ወረዳዎች ለስፖርት ክለባችሁ እንዳይወዳደሩ ለምን ተከለከሉ ብዬ ለፃፍኩላቸዉ ፅሁፍ መልስ ሳይመልሱልኝ አድፍጠዉ ቀሩ። ከመካከላቸዉ በጣም የምቃረበዉ ጓድኛዬን በግል ስጠይቀዉ በባሕላችን ደንብ ልጃችን ስንድር ማጫ ስለሚገባት አራቱን ወረዳዎች ለመለስ መርቀንላታል ብሎ አፌዘብኝ። ፌዙ ያለ ወቅቱ ስለሆነና ከእሱ አፍ ይህን በመስማቴ አባባሉ አስቆጥቶኝ ለብዙ ዓመታት የቆዬዉ ጓድኝነታችን እንደ ነበረዉ ሳይሆን በቀዘቀዘ መልክ ዘመናዊ የጥርስ ሰላምታ ተቀይሯል።

* ሥለ ክብርት እናታችን ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ አገር ወዳድነትና ጀግንነት የሚገልፅ እንደ ምሳሌ አድርገዉ  ያቀረቡት፦**ፋሽሽቱ መለሰ ዜናዊና አዜብ የእህታቸዉ ልጅ ቴሌፎን ደዉለዉ** በትግርኛ ሲያነጋግሯቸዉ ጀግናይቱ በአማርኛ ብቻ ነበር የሚመልሱላቸዉ ብለዉ አጋነዉ ፅፈዉታል:: አርበኛዋ እናታችን የቋንቋ ጥላቻ የላቸዉም:: ከትግርኛ ይልቅ በአማርኛ ማስረዳቱ ስለሚቀላቸዉ ብቻ መሰለኝ ምክንያቱ። እንደ እርስዎ አገላለጥ ግን ብዙ ሰዉ የተለያየ ትርጉም ሊሰጠዉ ይችላል:: ልክ እኔን የወያኔ ቃል ሳታስበዉ ተጠቅመሃል እንዳሉኝ እርስዎም በጀግናዋ አመሃኝተዉ የወያኔን ቃል ተጠቅመዋል ብዬ ብከስ ከእኔዉ በሬ ወለደ አይነቱ ክስዎ ተመሳሳይነት ያለዉ መሆኑን ለመጠቆም ያቀረብኩት ምሳሌ ነዉ። የወይዘሮ ማንሃሎሽ ጎላ አገር ወዳድነት በእርስዎ ልፈፋ ብቻ ሳይሆን የሚታወቁት በብዙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን እዉቅና ያተረፉ አርበኛ እናት ናቸዉ። ለወደፊቱም የታሪክ ባለፀጋ እንደመሆናቸዉ መጠን በታሪክ ፀሃፊዎች ማሕደር መመዝገቡ አይቀሬ ነዉ። ለሰዉ ልጅ ትልቁ ስጦታዉ በመልካም ተግባር የታሪክ ባለቤት ሲሆን ብቻ ነዉ።  ይሄዉና የሚወዷትና የሚናፍቋት አገራቸዉ እንዲህ ሁና ማየቱ ስላስጠላቸዉ በዚሁ እድሜአቸዉ ስደቱን የመረጡት።

* በኮለምበስ ያሃዮ ለተፈጠረዉ ችግር (**ጀርባሕን ሰጥተሃል ላሉት**)ከእዉነት የራቀ አባባል ነዉ::

ሆኖም ከእኔ የበለጡ ጠንካራ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን፤ወንድሞቼና እህቶቼ እንኳንስ ለሁለት ወይንም ከስሦት ለማይበልጡ ለሆዳቸዉ ያደሩ ከሃዲዎች ይቅርና በሺዎች ለሚቆጠሩ አፍ ማዘጋት የሚችሉ መኖራቸዉ ስላረጋገጥኩ ነዉ። እኔም ካለሁበት ሆኘ ድጋፌና ምክሬ ተለይቷቸዉ አያዉቅም:: ገፉ ካለም በቦታዉ በመገኘት ግዴታየን እየተወጣሁ ነዉ። እንግዲህ የማደርገዉ ግላዊ እንቅስቃሴዬ ሁሉ ለእኔ ማሳወቅ አለብሕ ማለትዎ ከሆነ ያለነበት ቦታ አሜሪካ መሆኑን እንዳይዘነጉት አደራ - የመለስ ቤተመንግስት አዲስ አበባ አይደለም  በዱላ ሃይል ሕዝባችን ያልሰማዉ ያላየዉ በግድ የሚናዘዝበት።

* ከፋኝ የተመሰረተዉ በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ልጆች ነበር የሚሉ አሉ ላሉት አጭር አገላለጥ በጣም ነበር ያፈርኩት:: ለምን ቢሉ በአከባቢዉ የቆየዉ ችግርና ስቃይ እንኳንስ እርስዎ በአካባቢዉ የነበሩና ያደጉ ይቅርና በርቀት ተከልሎ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ እንኳ ግልፅ የሆነለት ጉዳይ ነዉ። ሥለዚህ **ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም** ነዉ። የሰዉ ልጅ አስተዋይና አዋቂ መሆን የሚችለዉ ሲፈጠር ሳለ ይዞት የሚመጣ እውቀት ብቻ አይደለም። ከሱ በፊት ተፈጥረዉ የጻፉትን መፅሃፍ በማንበብ፣ በመጠየቅና በመመራመር መሆኑ ሁላችን የምንዘነጋዉ አይመስለኝም::  ታድያ ወንድም አማረ ከጫፍ እስከ ጫፍ የአራቱን ማዕዘናት ታሪክን በኮሶም ይሁን በማር ለዉሰዉ ማስነበብ የሚችሉ ምነዉ በተወለዱበት አካበቢ ለሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ባይትዋር ሆነዉ (**ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ አይነቱ**) ትንታኔ ለመጻፍ ተገደዱ። እኔ እንደገመትኩት ከፍተኛ ግፍና በደል በተፈጸመበት አካባቢ **ጀሮ ዳባ ልበስ ብለዉ** ቆይተዉ ይህችን በቅርብ ጊዜ የፃፏት የንዋይ ማመንጫ መጽሃፎ ለማሳተም ሲዘጋጁ አልፎ ሃጅ አግኝተዉ ጠይቀዉ ያገኟት በራሪ ቃል ብቻ የከፋኝን ታሪክ ይህን ይመስላል ማለቱ በጣም አሳፋሪ አገላለጽ ነዉ። ስለ ከፋኝ ብዙ የሚያዉቁት ነገር ከለለም ስም ማዉሳቱ አግባብ አልነበረም::  በዚህ ድርጅት ስም ብዙ ጀግኖች ደማቸዉን አፍስሰዋል። እርስዎም ግዜ ወስደዉ ሃቁን ማስፈር ይገባዎት ነበር ዘጊቶ የደረሰን ዜና መሆን አልነበረበትም።

እንግዲህ ከፋኝ ሲቋቋም አብሬ መስራች ነበርኩ ብየ ያላደረኩትና ያልዋልኩበት ጉዳይ ሜዳ ላይ ባቅራራ እንደ ስንቅ እያደርኩ የምቀለዉ እኔዉ ራሴ እሆናለሁ ማለት ነዉ። ለምን እንደተቋቋመና ስሙን ከፋኝ ብሎ እንደሰዬመ የምስተዉ አይመስለኝም። ሥለዚህ በእርግጠኛ ለመናገር ከፋኝን ያቋቋሙት በወልቃይት አካባቢ ተወለደዉ ያደጉ ጀግኖች ኢትዮጵያዉያን እምቢኝ ለጠባብ ብሂርተኛና ለተገንጣዮች የሚል መፈክር አንግበዉ የተነሱ የአርበኞች አምባ ናቸዉ። በቦታዉ ከነበሩ አርበኞች ጠይቄ እንደተረዳሁት ከፋኝ ሊቋቋም የቻለዉ በወቅቱ በወልቃይት አካባቢ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የሕብረ ብሔር ድርጅቶች(ኢሕአፓና ኢድዩ)ወያኔ ከአካባቢዉ ገፍትራ በማስወጣት በበላይነት ለመቆጣጠር በተደጋጋሚ በከፈተችዉ ጦርነት በለስ ቀንቷት ወልቃይትን ተቆጣጠረች። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነበር እነዚህ ጀግኖች ልባቸዉ ለመሸፈት የቆረጠዉ::  ምክንያቱም ያታግሉናል ብለዉ የተማመኑባቸዉ ድርጅቶች ተዳክመዉ ወደ ሌላ ቦታ ሲሸሹ አማራጭ ብለዉ የወሰኑት ዉሳኔ በጎበዝ አለቃ ተደራጅተዉ ልክ አንደ አለፉት አያቶቻቸዉ እምቢኝ ለፋሽሽቱ ጣልያን ብለዉ በአደጉበት በረሃ እየተሽለኮለኩ ሃያሉን የዉጭ ወራሪ እንዳባረሩት ያሁኖቹ ጀግኖችም በጣልይን ምስል የተዋቀረችዉ አደገኛ ጠላት ወያኔ የጥፋት መልዕክተኛ ለመሆኗ ከመላዉ ኢትዮጵያዊ በይበልጥ ከወርቅ የተነጠረ ልዩ ህዝብ ነዉ ብላ የተመጻደቀችለት የትግራይ ሕዝብን ከሕጻን እስከ ሽማግሌ ያለ ርህራሄ የምትጨፈጭፍ ድርጅት መሆኗ ባሻገር ሆነዉ ይመለከቷት ስለነበርና ወልቃይት እንደተቆጣጠረችም በቂም በቀል ሰበብ እያፋለገች ይቃወሙኛል ብላ የምትጠረጥራቸዉ አፍና መግደልና ማሰር ስትጀምር መብቱ የተነጠቀዉ ወገናቸዉን ለመከላከል የግዴታ መሳርያ አንስተዉ መታገል ጀመሩ። ወያኔም መፈጠሯ እስከምትጠላ አልመዉ በመተኮስ ያርበደበዷት ጅግኖች ናቸዉ። ወያኔ በሰራዊት ብዛት ያን አካባቢ ትቆጣጠር እንጅ ለአስር ዓመታት በነዚህ ብርቅዬ የአካባቢዊ የጎበዝ አለቆች የቁም ስቃይ እንደደረሰባት ባሳለፈችዉ ታሪኳ ልትረሳዉ የማትችል ከባድ ቅጣት እንደሰጧት የአካባቢዉ ኗሪ ሕዝብና ከድተዉ ከወጡት አባሎችዋ በዘግናኝነት ሲያስታዉሱት ሰምቼ

አለሁ። ወያኔ የታንክ አፈሙዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ደግና መግዛት እንደጀመረችም እነዚህ ጀግኖች የመሳርያ ጋጋታ ሳይበግራቸዉ በአገኙት አቅም እስከ አሁኗ ሰዓት በቆራጥነት ወያኔን እየታገሏት ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል አንዳንዶቹን ጀግኖች የሚወዷት ሂወታቸዉ ለአገርና ለወገን ሲሉ ከተሰዉት መሃል ለመጥቀስ ፦

*** ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሁለት**
**አለነ ክንድሺህ ታሪክ የሰራበት**
**አደ ህርዲ ላይ ተወልዶ ካደገበት።**
**ከፋኝ እምቢኝ አሻፈረኝ**
**የአገሬ አፈር ምስጡ ይብላኝ**
**ባዶ ስድስት ወስደዉ ከሚቀብሩኝ።**

**ቃብትያ አዲ ሕርዲ የፈሰሰዉ ደም**
**እንደ ጨቀዬ ነዉ ገና አልደረቀም**

በማለት ከወገኖቹ ጋር ሆኖ ቁጥራቸዉ ከሰባ የማያንሱ የወያኔን ቅጥረኞች መሃል ቃብትያ ላይ ከቦ ከገደለ በኋላ ከአስራ ሁለት ጀግኖች አጋሮቹ ጋር አብሮ ተሰዋ ስለዚህ  መላዉ ኢትዮጵያዊ የነዚህ ጀግኖች ሞያ በተግባር የሚዘክርበት ቀን እሩቅ አይሆንም ያዉም በታወቁ ታሪክ ፀሃፊዎች።

*** ይሄዉና የከላሽን አረር**
**መች እጁን ይሰጣል የቴዲ ዘር**
**አጭዶ ጣላቸዉ እንደ ጎመን**
**አርአያ መንግስቱን ባለ ድርብ ዝናር፦**

ይህም ነበሩ ከሚባሉት አንዱ ሲሆን ወያኔዎች የሚፈሩትን አፍነዉ ለመግደል ወደሚኖርበት አካባቢ ትጥቁን ለማስፈታት በዘመቱበት ግዜ ጀግናዉ ወጣት ወገኑንና እትብቱ የተቀበረበት የትዉልድ ቦታዉ ለዘራፊዎችና ለተስፋፊዎች አሳልፌ ከምሰጥ ሞቴን እመርጣለሁ ብሎ የቻለዉን ያህል ረፍርፎ የወደቀ ጀግና ኢትዮጵያዊ ነበር። አንድ ትልቅ ነገር መታወቅ ያለበት ብዛት ያላቸዉ ወጣቶች አገራችን በወያኔ ግፍ የቁም ስቃይዋን ከምናይ ገድለን ዕንሙት የሚል ቆራጥ መልእክት አስተላልፉዉ ሂደዋል እኔም ልጨምርበት የምፈልገዉ ነገር ቢኖር ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የተረከብነዉ ክብራችንን በደደቢት የቀን ጅቦች ተዘርፈን እንደ ዉሻ ፍርፋሪ ይጣልልኛል ብሎ አይኑ እንደሚቀላዉጠዉ ሆነን ከምንኖር ያለን አማራጭ ወያኔን ማስወገድ ብቻ ነዉ። የሽዎቹን ጀግኖች ደም የጎረፈበት መሬት ለመመራት ብላችሁ የዜናዊ ልጅ የጻፈላቸዉ ህግ መልሰዉ ማንበብ ለማይችሉት ደንቆሮዎች በወልቃይቴ ስም የጫማ እግራቸዉ ለምትስሙት በሙሉ የሙታን ደም ከርፍቶ እንደሚያሳብዳችሁ አትጠራጠሩ።

*** ብኢዱ ወንድማገኝ ተሎ ድረስ ትፈለግ አለህ**
**ወገንህ ተሰቃይቷል ድምፅ ስላጠፍህ**
**በምታዉቀዉ በረሃ መግብያ ተጠቅመህ**
**አድነን እንላለን ወንድም እህቶችህ**
**ከነብሰ በላ የወያኔ ጅቦች፦**

ከወጣትነት እድሜዉ ጀምሮ ልበ ሙሉ ለሚያዬዉና ለሚመለከተዉ የጀግንነት ግርማና ማእረግ የነበረዉ። ያ የወንድነት መለክያ ግዜ እንደመጣም ብኢዱ እንደሌሎች አርበኞች በሚያዉቀዉና ተወልዶ ባደገበት በረሃ ተገን አድርጎ ወያኔን የደም እንባ እንድታነባ ካደረጉት የጀግኖች ጀግና መሃል አንዱ ነበር። ወያኔዎች የጥፋት ተልእኳቸዉ ተግባር ላይ ለማዋል ሲላኩ ከመሪዎቻቸዉ የሚሰጣቸዉ ምክር ተጠንቅቃችሁ ሂዱ ያ ተካል ብኢዱ እንዳያገኛችሁ ብለዉ እንደሚያስጠነቅቋቸዉ የሚያዉቁና

የሰሙ አዉርተዉኛል። መቸስ ጀግናና ቆራጥ እድሜዉ አጭር ነዉና ብዛት ያለዉን ጠላት አስተኝቶ የሂወቱ ፍፃሜ ሆኗል። ከዚሕ ጀግና ጋር ሆነዉ ለአገራቸዉና ለወገናቸዉ ክብር ሲሉ ብዙ ወንድሞቹና ያክስት ያጎቶቹ ልጆች አብረዉ ወድቀዋል በሂወት የተረፉትም ንብረታቸዉና ርስታቸዉ ተቀምተዉ ለስቃይና ለችግር ተዳርገዋል። ይህ ሁሉ በደል ሊፈፀምባቸዉ የቻለዉ እኛን ከወራሪዎች ለመከላከል ሲሉ እንጅ ለግል ጥቅማቸዉ ብለዉ አይደለም። ይህ ብልሹ ዘመን አልፎ ጀግኖች በግልፅ የምናመሰግንበት ወቅት እስከሚመጣ ድረስ ሁላችን ክቡር የሆነዉን መስዋእትነታቸዉን ለማስታወስ ሻማ እያበራን  እንዘክራቸዉ አለን።

*** ሶላ አፋፍ ላይ መልካም ስጋ ተበላ**
**በአበበ ተመትሮ በመሰለ የተቆላ**
**አገር ሰላም ሲሆን ወሬዉ ሲደራ**
**ታሪክ ያስታዉሳችኋል የኋላ ኋላ**
**እንደነ ቴዎድሮስ አሉላ አባነጋ።**

ከአንድ ቤተሰብ የተፈጠሩ-መሰለ፣አበበና ደመቀ ይርጋ የተባሉት ጀግኖች ወንድማማቾች ወያኔ በሚያደርሱባት ከባድ ጥፋት በአካባቢዉ እንደ ልቧ የፈለገችዉን እንዳታደርግ እንቅስቃሴዋን ከገቱት የአካባቢዉ ጎበዞች ዋናዎቹ ነበሩ። እነዚህ የራስ ምታት የሚሰጧትን አድኖና ገድሎ ለሚያመጣላት ሹመትና ገንዘብ ለመስጠት ጥሪ ስታደርግ አንድ ለሆዱ ያደረ የአክስታቸዉ ልጅ እኔ ለዚሁ ግዳጅ ብቁ ነኝ ብሎ ቀረበ። ይህ ያክስታቸዉ ልጅ ወያኔ በደል እንደበደለችዉና ከነሱ ጋር ሆኖ ሊታገላት እንደወሰነ አድርጎ መልዕክት ይልካላቸዉና ወደ ሚንቀሳቀሱበት ሶላ ከተባለዉ ቦታ ሂዶ ይገናኛቸዋል::  ከኋላዉም ወያኔዎችም ለመክበብ በርቀት ተከትለዉታል:: የከበባዉ ስአት አንደተቃረበም ራሱ ተኩስ ከፍቶ አንዱን ዘመዱ ሲገድል አበበ ይርጋ አዙሮ እሱን ገድሎ ከመጣዉ ወራሪ ጦር ጋር ዉግያ ተጀምሮ ከበባዉን በአንድ በኩል ሰብረዉ ወጡ። ከመንደሩ እንዳይታኮሱ ብዙ ሕፃን፣ ሴትና ሽማግሌ አናስጨርስም ብለዉ ሸሽተዉ ከመንደሩ በጣም ርቀዉ ወጥተዉ ከአንድ ገኸ ቦታ ጠብቀዉ ይቆዩና ገጠሟቸዉ ከሄዱት 74 የወያኔ ወታደሮች  71ዱን ገድለዉ ጀግኖቹ ወንድማማቾችም እዛዉ ተሰዉ። ሦስት የወያኔ ተዋጊዎች አምልጠዉ ቃብትያ ሲገቡ የት አለ ቀሪዉ ሰራዊት ብለዉ ሲጠይቋቸዉ የወጣ የለም ሁሉን ጨርሰዉታል ሲሏቸዉ ከወያኔዎቹ አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ኡኡታዉን አሰማ። ወያኔን መርቶ የወሰደዉ እናት የልጇ መሞት ሰምታ ከቤቷ ሆና ስታለቅስ የሦስቱ ጀግኖችም እናትም ተደብቃ ከቤቷ ጓሮ ሆና ስታለቅስ አንድ የወያኔ ባለስልጣን ለምን እንደምታለቅስ ሲጠይቃት ከእናንተ ጋር ተታኩሰዉ የሞቱት ልጆቼ ናቸዉ ስትለዉ በይ ልጆችሽ ሲሰርቁ ወይም ሲያጭበረብሩ አልሞቱም ለቆሙለት አላማ ነዉ የሞቱትና እንደ እህትሽ ከቤትሽ ሆነሽ እዘኝ ብሎ እንዳላት እማኞች አጫዉተዉኛል።

*** ግንባሩን የሚሰጥ ለቆመለት አላማ**
**የሃይሉ ልጅ የተሰማ**
**ፈርዶ ሰቀለዉ የወያኔን አሳማ**
**ጠላቱን የሚያቀልጥ አንደ ሻማ**
**ላደገበት ለተወለደበት ባድማ**
**ያ ተስፋይ ሃይሉ ኢትዮጵያዊዉ ጀግና ፦**

አቶ ተስፋይ ሃይሉ ለኢትዮጵያ ህልዉናና ነፃነት በተደረጉት ትግሎች አዋጊና ተዋጊ በመሆን ብዙ የጀግንነት ሥራ የሰራ ነበሩ ከሚባሉት የወገንና የአገር አለኝታ አንዱ ነበር ። አዲ ጎሹ ላይ በዋለዉ ጦርነት ግንባር ቀደም ሆኖ በመግባት በጀግንነት ሞያ የሂወቱ ፍጻሜ ሆነ ከሱ ጋርም የአካባቢዉ እዉቅ ጀግኖች ተሰዉተዋል።

* ወያኔ በእግሯ መዳፉ ረግጣና አፍና በወልቃይት ህዝብ ላይ ያደረሰችዉ በደልና አሁንም እያደረሰችዉ ያለዉ ሁሉ ዘርዝሮ ለሚመለከተዉ የሚያሰማ ወገን በመታጣቱ ነዉ እንጅ በዚህ አካባቢ የተደረገዉ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ይህ ነዉ ተብሎ በአጭር ፅሁፍ ብቻ የሚገለፅ አይደለም ። ለታሪክ ፀሃፊዎችም ሆነ ለእንባ ጠባቂ ድርጅቶች ይህን እድል ተጠቅሜ የማሳስበዉ ነገር ቢኖር በዚህ ህዝብ ላይ ለሚፈጸሙት ተደራራቢ ግፍና በደሎች ዐይንና ጆሮቻችሁን እንድትከፍቱ ደግሜ አሳስባለሁ። በዚህ አካባቢ ተወልደዉ ያደጉት የአካባቢዉን ሁኔታ በይበልጥ ስለሚያዉቁ ለምትጠይቁት ጥያቄ ሆነ ለማንኛዉ ነገር ተባባሪ የማይሆን አለ ብዬ አልገምትም አንድ ወይም ሁለት ቢገጥሟችሁም እንዳትደናገጡ ሁሉ አገር ወዳድ ሊሆን አይችልም እንደ ሌላዉ አካባቢም ለሆዳቸዉ ያደሩ ጥቂት የወያኔ ፍርፋሪ ለቃሚዎችም እንዳሉን ማረጋገጥ እወዳለሁ።

* ለተከበራችሁ ይህችን አጭር መልስ ያዘለች ፅሁፌን ለምታነቡ ወንድም እህት በሙሉ ሳላዉቅ በስህተት አላስፈላጊ ቃል ተጠቅሜ ከሆነ አርማችሁ እንድታነቡልኝ ከይቅርታ ጋር በማክበር እጠይቃለሁ። ይህን ጽሁፍ ስጽፍ ማንንም ድርጅት ወይንም አካል ወክዬ አይደለም የግሌ አስተሳሰብ ለመሆኑ ደግሜ ደጋግሜ ማረጋገጥ እወዳለሁ። በሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን ጀግኖች ለወገናቸዉ መብትና ክቡር ሕይወታቸዉ ሰጥተዋል አሁንም ግብግብ አንደገጠሙ ናቸዉ። ከላይ በተናጠል የጠቀስኳቸዉ ጀግኖች ለምሳሌ ያህል አንጅ እነዚህ ብቻ ናቸዉ ማለቴ እንዳልሆነ ማሳሰብ እወዳለሁ:: ቀሪዉም ለወደፊቱ በሰፊዉ ይቀርባል::  ፅሁፌ አልተቋጨም ይቀጥላል። መፅሃፍ ፀሃፊዎችና ታሪክ መዝጋቢዎችም የአንድ አቅጣጫ ዘጋቢዉች ብቻ መሆን የለባችሁም:: ሁሉን ለመዳሰስ መሞከር ይኖርባችኋል:: አቶ አማረም ግለሰብን ሽሮ ቀጠነ ብለዉ ከመዉቀስ ተላቀዉ የወገን አምባ ጠባቂ እንዲሆኑ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ:: አመሰግናለሁ።

ኢትዮጵያችን በጀግኖች ልጆችዋ መስዋእትነት ለዘልዓለም ተከብራ ትኖራለች!!